# ምድብ 5 (ከ10ኛ - 12ኛ ክፍል)
## 8 ኛ ሳምንት
## የዳዊት በደል ውጤቶችና የንስሐ ሕይወት

**ዓላማ**

- የኃጢአትን ምክንያቶችና የሚያስከትሉትንም ውጤቶች በመግለጽ በእግዚአብሔር ፊት የተወደደ ስለሆነው ወይም ተቀባይነት ስላለው የንስሐ ሕይወት መገንዘብ።

**ጥቅስ**

- “አንተን ብቻ በደልሁ በፊትህም ክፋትን አደረግሁ።”

**ምንባብ**

- በትምህርቱ ውስጥ የተጠቀሱትን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ማንበብ።

**መግቢያ**

- 2ኛ ሳሙኤል ምዕራፍ 11 ከቁጥር 1 እስከ ፍጻሜ አንብቡ።
- ዳዊት ከብዙዎች ወንድሞቹ መካከል በእግዚአብሔር ተመርጦ ነበር። “እንደ ልቤ የሆነ ሰው ፈቃዴንም ሁሉ የሚያደርግ የእሴይን ልጅ ዳዊትን አገኘሁ አለ።” የሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 13 ቁጥር 22።

**የትምህርቱ ዝርዝር መግለጫ**

1. **በእግዚአብሔር ፊት የበደለባቸው ምክንያቶች አንተ ታላቅ ተራራ ሆይ እንዴት ወደቅህ**

**ዳዊት ከመንገሡ በፊት**

- ከሳዖል ፊት ይሸሽ ነበር የሚሸሸግበትም ሥፍራ ስላልነበረው ፈጽሞ በእግዚአብሔር ተደግፎ ነበር።
- ደፋር ወይም ጀግናና ብርቱ ነበር። በእግዚአብሔር ላይ ከነበረውም እምነት የተነሣ የእግዚአብሔርን ጠላቶች ለመዋጋት ዘወትር በመጀመሪያው መስመር ይሰለፍ ነበር።
- ጎልያድንም “እግዚአብሔር ዛሬ አንተን በእጄ አሳልፎ ይሰጣል እመታሀማለሁ።” ይለው ነበር። 1ኛ ሳሙኤል ምዕራፍ 17 ቁጥር 46።
- በነበረው በጥቂቱ በመርካት ያለኝም ይበቃኛል በማለት በነገር ሁሉ እግዚአብሔርን ያመሰግን ነበር። እግዚአብሔር የደስታውና የሐሴቱ ምንጭ ነበር።

**ዳዊት ንጉሥ ከሆነ በኋላ ሳይበድል**

- መንግሥቱ ስለተቋቋመለት በኃይሉ በብርታቱ ወይም በችሎታው የሚደገፍ ሆነ።
- ስለራሱ የሚያዝንና የሚተክዝ መሆን ጀመረ። ሕዝቦቹ ወይም ወገኖቹ ስለርሱ ለመዋጋት ወደ ጦርነት ሲወጡ እርሱ ግን በቤት መቆየትን የሚመርጥ ሆነ።
- የሚሠራውም አንዳችም ሥራ ሳይኖረው በሚያገኘው ጊዜ ሁሉ በመተኛት ለሰውነቱ ዕረፍትን የሚሰጥ ሆነ።
- ከሙሴ ሕግ በመውጣት የብዙ ሴቶች ባል ሆነ። ራሱንም በማሳት ጊዜያዊ የሆነ ምድራዊ ምቾትን ወይም መደላደልን የሚሻ ሆነ።

2. **እግዚአብሔርን መበደል**

- ክፉ ምኞት ወይም ሐሳብ ➔ መጥፎ ተግባር ወይም ዝሙትና ➔ ሰውን የመግደል ወንጀል።
- ዳዊት በዚህ ወቅት ተከታታይነት ባለው የንስሐ ሕይወት የሚኖርና የሚያስበውን ሐሳቡን ሁሉ እየመረመረ ኃጢአቱንም የሚናዘዝባትና የሚተዋት ቢሆን ኖሮ በበደል የሚገኝ ባልሆነ ነበር።
- ነገር ግን እጅግ መዝናናትን ስላበዛ መንፈሳዊነቱ እየዘቀጠ መሄድ ጀምሮ በታላቅ ኃጢአት ወድቆ ተገኘ። ይኸም መነሻው በክፉ ምኞት ወይም ሐሳብ የተጀመረ ነበር።
- ዳዊት ዓመቱን ሙሉ ስለኃጢአቱ ንስሐ መግባትን ሳይፈልግ ቆየ። ይልቁኑ የተቻለውን አጋጣሚ ሁሉ በመጠቀም ኃጢአቱን መሸፈን ይፈልግ ነበር። ይኸም አካሄዱ እጅግ የከበደውን ኃጢአት የመሥራት አሳልፎ ሰጥቶታል። 2ኛ ሳሙኤል ምዕራፍ 11 ከቁጥር 1 እስከ ፍጻሜ።
- ኦርዮ “ታቦቱና የእስራኤል የይሁዳ ወገኖች ሁሉ በጦር ሜዳ በጎጆ ተቀምጠው ልበላና ልጠጣ ወይም ከሚስቱ ከቤርሳቤህ ጋር ልተኛ ወደቤቱ አልሄድም።” በማለት የሚደነቅ ድርጊት በዳዊት ፊት ፈጸመ። ዳዊት ግን ይኸን የሚደነቅ ድርጊቱን እንደማድነቅ “ጽኑ ሰልፍ ባለበት በፊተኛው ሥፍራ አቁማችሁ ተመትቶ ይሞት ዘንድ ከኋላው ሽሹ።” የሚለውን የሞት ደብዳቤውን አሸክሞ በጦር ሜዳ ላለው ለኢዮአብ ላከለት። በዚህም ድርጊት በጦር ሜዳ ኦርዮ እንዲገደል በማድረግ ቤርሳቤህን ሚስቱ አድርጎ ወሰዳት ኃጢአት በሕይወታችን የሚያደርገው ይኸንኑ ነው። ራስ ወዳድና ምንም የማንመለከት ዕውራን ያደርገናል።

3. **ንስሐ 2ኛ ሳሙኤል ምዕራፍ 12 ከቁጥር 1 እስከ ፍጻሜ።**

- እግዚአብሔር ኃጢአቱን ገለጠለት ነቢዩ ናታንም በምሳሌ አስረዳው። እግዚአብሔርም ያ ሰው አንተ ነህ ..... የእግዚአብሔርንስ ነገር ለምን አቃለልህ? አለው። 2ኛ ሳሙኤል ምዕራፍ 12 ከቁጥር 7 እስከ 9።

- ዳዊትም "እግዚአብሔርን በድያለሁ" በማለት ተናዘዘ። ናታን ግን "እግዚአብሔር ደግሞ ኃጢአትህን አርቆልሃል አትሞትም።" አለው። 2ኛ ሳሙኤል ምዕራፍ 12 ቁጥር 13። ይህም እግዚአብሔር ንስሐ ለምትገባ ነፍስ ያለው ምሕረት ምን እንደሚመስል የሚያስረዳ ነው።
- እግዚአብሔርን ኃጢአትን እጅግ የሚጠላ ቢሆንም ርኅሩህና ፍቅርም ነው። ንስሐ ለገባች ነፍስ የሚያፈሰውን የፍቅር ጅረት እንዳይወርድ የሚገድበው አንዳች ነገር የለውም።
- ዳዊት ኃጢአቱን ተናዝዞ ንስሐ ሲገባ ወዲያወኑ እግዚአብሔር ይቅርታ አድርጎለታል። ይኸም የጠፋውን ልጁን መምጣት ይጠብቅ የነበረው ባለጠጋ እርሱ እግዚአብሔር ነው። የሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 15 ከቁጥር 18 እስከ 24።
- ዳዊትም "አንተን ብቻ በደልሁ በፊትህም ክፋትን አደረግሁ በማለት አብዝቶ አለቀሰ። መዝሙረ ዳዊት 50 ቁጥር 4።
- ዳዊት የቀረ ዘመኑን ሁሉ ስለኃጢአቱ ንስሐ በተሰበረ ልብ በእግዚአብሔር ፊት በመዘመር የመዝሙሩንም መጽሐፍ ቤተክርስቲያንና መላው ዓለም ሁሉ እንዲገለገልበት ቅርስ አድርጎ ተቶልናል። የሕይወቱም የመጨረሻ ዘመናት ከመጀመሪያው እጅግ የላቁ የበለጡ ነበሩ። ንስሐ ሆይ! ዘማዊውን ሰው ድንግል ያደረግሽው አንቺ ነሽ።

4. <u>ኃጢአት ያስከተላቸው ነገሮች</u>

- ለኃጢአቱ ይቅርታ ቢገኝም ኃጢአት ያሰከተላቸው ነገሮች ግን ተከታትለው መምጣታቸው የግድ ነው።
  1. ከቤትህ ሰይፍ ለዘላለም አይርቅም። ልጁ አቤሴሎም መንግስቱን የመገልበጥ ሙከራ አድርጓል። 2ኛ ሳሙኤል ምዕራፍ 12 ቁጥር 10።
  2. የተወለደልህ ልጅ ፈጽሞ ይሞታል። 2ኛ ሳሙኤል ምዕራፍ 12 ቁጥር 14።
  3. እግዚአብሔር ሚስቶችህን ወስዶ ለሉሎች ይሰጣል። 2ኛ ሳሙኤል ምዕራፍ 12 ቁጥር 11።
  4. ከቤትህ ክፉ ነገር ይነሳብሃል። 2ኛ ሳሙኤል ምዕራፍ 12 ቁጥር 11።
- ይሁን እንጂ የእግዚአብሔር ምሕረት ንስሐ የምትገባውን ነፍስ የኃጢአት ውጤት ወደ ሚያነጻ እሳትነት መለወጥ ይቻላል።
- ሰውነታችን ለመከራ ተላልፋ ብትሰጥም ነፍሳችን ግን በንስሐ በክብር አጊጣ በሰማያዊው መሹራ ፊት ትቀርባለች። መኃልይ ምዕራፍ 4 ቁጥር 1።

<u>ማጠቃላይ</u>

- ልባችን በእግዚአብሔር ፈቃድ የተሞላ ከሆነ ውጤቱ በጎ በረከት እና ሀብት ሲሆን ልባችን ግን በክፋትና በዚህ ዓለም ፈቃድ ብቻ ከተሞላ ግን ውጤቱ መጥፎ መከራ ማጨድ ይሆናል።

<u>ተግባር</u>

- ስለሚኖሩን ትርፍ ጊዜያት በማስተዋል ራሳችንንም ሆነ አእምሮአችንን አስፈላጊ በሆኑ መንፈሳዊ ሥራዎች የገዛን እንሁን። በአሉን ትርፍ ጊዜያት ሁሉ በቤተክርስቲያን ያሉ ማናቸውንም ሥራዎች እንሥራ። ባዶ አእምሮ ሁል ጊዜ የሰይጣናዊ ድርጊቶች ፋብሪካ ነው።
- ዘወትር የተመረጠ ሕይወት ለመኖር የምንሻ ከሆንን በየዕለቱ የምናስበው ሐሳባችንን፣ የምንሰማውንና የምናየውንም በተመለከተ ቁጥብና ጥንቁቅ እንሁን። ዓይናችንንም በመስቀል ላይ የተሰቀለልንን የመልካሙን እረኛ ሥዕል እንዲመለከት ብናደርገው የዚህን ዓለም ሥዕል ዘወትር ከመመልከት የተጠበቀ እንዲሆን እንረዳዋለን።
- የምንሰማው የምናየው ማንኛውም ክፉ ነገር በአእምሮአችን ይቀመጥና ሰይጣን የፈለገውን የሚፈጽምበት ድርሻው ሆኖ ይሰጠዋል። በደከምንም ጊዜ ያንኑ እያወጣ ሥዕሉን ያሳየንና እያሻሻለና እየለዋወጠውም በኃጢአት ለመውደቅ አሳልፎ ይሰጠናል።
- ነገር ግን ልባችን ዘወትር በመስቀል ላይ ወደተሰቀለው ወደ ጌታችን ሕይወትንም ወደሚሰጠው ቃሉ የሚያተኩር ከሆነ ዓለማዊ ለሆኑ ሐሳቦችና ክፉ ሥዕሎች ቦታ አይኖረውምና ልባችንን በተሻለው እንምራው።
- ቅዱስ ጳውሎስ እንደተናገረው ከኃጢአት ጋር እስከደም መፍሰስ ድረስ እንታገል። ቅዱሳን የምንላቸው እግዚአብሔርን ከመበደል ከማሳዘን ይልቅ ደማቸውን ማፍሰስ መሥዋዕት መሆንንም ያስቀድሙ ነበር።
- ዘወትር በንስሐ ሕይወት ታንጻችሁ የምትኖሩ ሁኑ።
- የእግዚአብሔር ፍቅር ለሰው ልጅ እንዳትደረግ የሚያቆመው አንዳችም ኃይል የለምና። በበደልን ጊዜ ሁሉ ኃጢአታችንን በመናዘዝ በእግዚአብሔር ፊት እንቅረብ። ንስሐ ወደ እግዚአብሔር የበለጠ የምንቀርብበት በእቅፉም የምንኖርበት በምድር እየኖርን የመንግሥተ ሰማያትን ሕይወት የምንቀምስበት ነውና።

**ይቆየን።**